# ምሥጢረ ጥምቀት

## የጥምቀት ምሳሌ በብሉይ ኪዳን

ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት የዳኑባት መርከብ የአማናዊቱ ቤተክርስቲያን ምሳሌ መሆንዋ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ነው፡፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር በልቡናቸው ያደረው ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ሲድኑ እግዚአብሔርን ድምፅ ያልሰሙት የኖኅ ዘመን ለአማናዊው ጥምቀት ምሳሌነት እንዳለው ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ሲገልጽ (ሲያስተምር) #ጥቂቶች ማለትም ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም፡፡ ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድናል፡፡ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ$ 1ጴጥ.3÷20-12፡፡

ኖኅና ቤተሰቡ የዳኑባት መርከብ ምሳሌዋ በሆነው በአንዲቱ ቤተክርስቲያን የሚደረገው ጥምቀት ከፍዳ ያነጻናል ከዲያብሎስ ቁራኝነት ያላቅቀናል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ድኅነት በጥምቀት መሆኑን ሲገልጽ ይህም ውኃ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድናል ብሏል፡፡

### 1. ግዝረት

ከፍ ብለን እንደገለጽነው፣ ግዝረት የእግዚአብሔር ሕዝብ መለያ ምልክት ነበር፡፡ ያልተገረዘ ሁሉ የአብርሃም ልጅ አይባልም ነበር፡፡ ከሕዝቡም ተለይቶ እንዲጠፋ እግዚአብሔር አዝዞ ነበር (ዘፍ.17 ቁ. 14)፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ ማለትም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡ ጽኑ ፍዳ ወዳለበት ገሃነም ይወርዳል እንጂ፡፡ ምክንያቱም መንግሥተ ሰማይ ካልገባ ያለው ምርጫ ገሃነም መጣል ነውና (ዮሐ.3÷3-6)፡፡ ስለዚህ ግዝረት ለሕዝበ እግዚአብሔር ግዴታ እንደነበረ ሁሉ ጥምቀትም ለክርስቲያኖች ሊፈጽሙት የሚገባ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው፡፡

ግዝረት ሊመጣ ላለው ለጥምቀት ምሳሌው መሆኑን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ ‹‹በክርስቶስ ግዛሪነት የኃጢአትን ሕዋስ ሰንኮፍ ቆርጦ በመጣል ሰው ሠራሽ ያይደለ ግዝረትን የተገዘራችሁበት፤ በጥምቀት ከእሱ ጋር ተቀበራችሁ፣ ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በእግዚአብሔር ረዳትነትም በሃይማኖት ከእሱ ጋር ለመኖር በእስዋ ተነሣችሁ›› ብሏል (ቈላ.2÷10-12)፡፡

ግዝረት ማለት ከአካል ላይ ሥጋን ቆርጦ መጣል እንደሆነ ሁሉ ጥምቀትም ሐዋርያው እንዳስተማረን የኃጢአትን ሰንኮፍ ከሕይወታችን ቆርጦ መጣል (ማስወገድ) ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ግዝረት በሰው አማካኝነት የሚፈጸም ሲሆን የኃጢአት ሥሩ ተቆርጠ ተመንግሎ የሚጣልባት ጥምቀት ደግሞ በካህናት አማካኝነት ይፈጸማል፡፡ ዳሩ ግን የኃጢአትን ሰንኮፍ ቆርጦ ከሕይወታችን የሚያስወግደው (የሚጥለው) በስሙ አምነን የተጠመቅንበት መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ነው፡፡ **በሰው እጅ ያልተደረገ በክርስቶስ ገዛሪነት የኃጢአት ሥር ተቆርጦ የሚወገድበት ግዝረት ጥምቀት ነው፡፡**

አንድ ሰው ሲገረዝ ከአካሉ ደም ይፈሳል፡፡ እደዚሁም ሁሉ በክርስቶስ ደም የተዋጀን ክርስቲያኖች ከኃጢአታችን የታጠብንበትን የጌታ ደም በጥምቀት እናገኘዋለን፡፡ ግዝረት ከአንድ ጊዜ በላይ እንደማይሆንና ሊደገምም እንደማይችል ሁሉ ጥምቀትም የማትደገም፣ የማትከለስ አንዲት ናት፡፡ ሁለት ጊዜ መጠመቅ አይቻልም (ኤፌ.4÷5)፡፡ መጠመቅ ከክርስቶስ ጋር በሞቱ መተባበር ነው (ሮሜ.6÷8)፡፡ ጌታ የሞተው አንድ ጊዜ ነውና ጥምቀትም አንድ ጊዜ ነው፡፡

## 2. የእሥራኤል ባሕረ ኤርትራን ማቋረጥ

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እንዲህ ሲል ገልጦታል ‹‹ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፡፡ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፡፡ ሁሉም ሙሴ ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ›› (1ቆሮ.10÷1-12)፡፡

እሥራኤል ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር እንደተጠመቁ እኛም አንድነታችን በደሙ ከኃጢአታችን ካጠበን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዲሆን እንጠመቃለን፡፡ እስራኤል ከዘመናት የባርነት ቀንበር የተላቀቁትና ነፃ የወጡት የኢርትራን ባሕር ተሻግረው ነው፡፡ ከኃይለኛው ከፈርዖን እጅ የዳኑትም የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ነው፡፡ የኤርትራ ባሕር ለፈርዖንና ለሠራዊቱ ሞትን ሲያስከትልባቸው ለእስራኤል ግን ሕይወት፣ ደስታ፣ ነፃነትን አጎናጽፏቸዋል፡፡

እኛም ለርኵሳን አጋንንት ከመገዛትና ከፍዳ፣ ከመርገም፣ ከዘላለም ሞት፣ ነፃ ምንሆነው በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን ስንጠመቅ ነው፡፡ የኤርትራ-ባሕር ለፈርዖንና ሠራዊቱ መጥፊያ እንደሆነ በጥምቀትም አጋንንት ድል ይመታሉ፡፡ ለዚህ ነው በሥርዓተ ጥምቀታችን ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ ከምዕራብ (ሲዖል) ወደ ምሥራቅ (ገነት) የሚዞረው፡፡

የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አለቃ ንዕማን ከለምጹ የነጻው በዮርዳኖስ ወንዝ ታጥቦ ነው፡፡ በነቢይ በታዘዘው መሠረት በዮርዳኖስ ውኃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማለት ታጥቦ ሥጋው እንደገና እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ንጹሕም ሆኖ መመለሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኘዋለን (2ነገ.5÷8-14)፡፡

እኛም ከኃጢአት ደዌ የምንነጻውና ያረጀው ሕይወታችን ሊታደስ የሚችለው በጥምቀት ነው፡፡ ስንጠመቅ የክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን እንዳጠበን ማረጋገጣችን ነውና፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት እንዲህ ብሏል ‹‹በውኃም አጠብሁሽ፤ ከደምሽም አጠራሁሽ፤ በዘይትም ቀባሁሽ›› (ሕዝ 16÷9)፡፡

ለጊዜው ይህ አነጋገር በኃጢአት ለተመላችው ለኢየሩሳሌም የተነገረ ቢሆንም ፍጻሜው ግን በኃጢአት ለተበላሸው ለሰው ሁሉ ሕይወት የተነገረ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ‹‹ባንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ እነሆ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበር፡፡ እኔም መጎናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ፡፡ ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽም፡፡ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡ አንቺም ለእኔ ሆንሽ፡፡›› (ሕዝ 16÷8)፡፡

እግዚአብሔር በምሕረቱ ሰውን በጎበኘበት ወቅት በፍጹም ፍቅሩ ስቦ ነው የሰውን ልጅ ያቀረበው፡፡ ጌታችንም እርቃኑን በመሰቀል የእኛን ከኃጢአት መራቆት አስቀርቶልናል፡፡ የክብር የሕይወት መጎናጸፊያ አጎናጽፎናል፡፡ ስለ እኛ መከራን ተቀበለ፡፡፡ የእርሱ አደረገን፡፡ ‹‹በውኃ አጠብሁሽ›› የሚለው ‹‹ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድን›› ያስረዳናል፡፡ ይኸውም በጥምቀት ነው፡፡ በጥምቀት ከዘላለም የኃጢአት ባርነት መላቀቃችንን ሲያስገነዝበን ‹‹ከደምሽም አጠራሁሽ›› ብሏል፡፡ በተጨማሪም ጥምቀት በቅብዐ ሜሮን ማንተምነት እንደሚጸም ‹‹በዘይትም ቀባሁሽ›› በማለት አረጋግጦልናል፡፡ ‹‹አንቺም የእኔ ሆንሽ›› እንዳለው ሁሉ ተጠማቂውም በጥምቀት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመውን የቤዛነት ሥራ ሁሉ አግኝቶ የእርሱ ወገን መሆኑን ያስረዳል፡፡